# *“ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ”*
# *የውድድር ሕጎች*

## ***<u>አንቀጽ 1፡ የውድድር አዘጋጅ</u>***

“ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ” ውድድር ሲሆን (ከዚህ በኋላ “ውድድር” ተብሎ የሚታወቅ) ውድድሩ በአዝል 2 ላይ ስማቸው በተዘረዘረው በአጋሮች ስም እና እንደ አጋሮች (ከዚህ በኋላ በአንድ ላይ “አጋሮች” እና “አዘጋጆች” በተናጠል ደግሞ “አዘጋጅ” ተብለው የሚታወቁ) በመሆን የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 24 ኮር ሚሼሌት፤ 92800 ፖቴዥ፤ ፈረንሳይ በሆነው እና በቁ 542 034 921 (ናንቴሬ የንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ) በተመዘገበው እና በአዘጋጆች ስም እና እንደ አዘጋጆች በመሆን በሚሰው የፈረንሳይ /የጆይንት ስቶክ ኩባንያ/ (ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር) በቶታል ማርኬቲንግ ሰርቪስስ የተዘጋጀ ነው፡፡

ውድድሩ ከጥር 1/2014 ዓ.ም እስከ ጥር 29/2014 ዓ.ም ካሜሮን ውስጥ ከሚካሄደው የቶታልኢነርጂስ የአፍሪካ ዋንጫ 2021 የእግር ኳስ ውድድር ጋር በተያያዘ በቶታልኢንርጂስ የማደያ ጣቢያዎች የአዘጋጆች ኔትወርክ አማካኝነት የሚዘጋጅ እና ማስተዋወቂያዎች የሚሰሩበት ይሆናል፡፡

ውድድሩ በነዚህ ሀገራት ውስጥ በየራሳቸው ብቸኛ ኃላፊነት በየተመዘገቡበት ሀገር ውስጥ በአዘጋጆቹ የሚንቀሳቀስ ይሆናል (ከዚህ በኋላ በነዚህ ህጎች እዝል 1 ላይ “ተሳታፊ ሀገራት” ተብለው የሚታወቁ)፡፡

ለነዚህ ህጎች ተፈጻሚነት አላማ ሲባል ከቶታልኢነርጂስ ኤስኢ ጋር በተያያዘ “አጋር” የሚለው ቃል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በቶታልኢነርጂስ ኤስኢ ቁጥጥር ስር የሚገኙ ሁሉንም ድርጅቶች ማለት ይሆናል (“ቁጥጥር” የሚለው ቃል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከ50% በላይ የድምጽ መስጠት መብትን መያዝ ሲሆን፤ “በቁጥጥር ስር የሚገኙ”፤ “መቆጣጠር” “በቁጥጥር ስር ማድረግ” የሚሉት ቃላትም እያንዳንዳቸው እንደዚሁ ይተረጎማሉ፡፡)

## ***<u>አንቀጽ 2፡ የሕጎቹ አላማ</u>***

እነዚህ ሕጎች (ከዚህ በኋላ “ሕጎች” ተብለው የሚታወቁ) ይህንን ሰነድ እና እዝሎቹን የሚያካትቱ ሲሆን በውድድሩ ተሳትፎ የማድረጊያ ገዢ ደንቦችን እና ሁኔታዎችን እንዲሁም የውድድሩ የአሰራር ሂደት ገዢ ደንቦችን እና ሁኔታዎችን የሚያስቀምጡ ናቸው፡፡

እያንዳንዱ አዘጋጅ በራሱ ስም እና እንደ እራሱ በመሆን አግባብነት ባለው ተሳታፊ ሐገር ውስጥ ውድድሩን ያዘጋጃል፡፡ በተለያዩ ተሳታፊ ሐገራት መካከል የጋራ እና የጣምራ ተጠያቂነት በአዘጋጆቹ ላይ አይኖርም፡፡

በእያንዳንዱ ተሳታፊ ሀገር ውስጥ በተሳታፊ ሐገር የተመዘገበ አዘጋጅ አግባብነት ባለው አዘጋጅ ሐገር በሚገኙ የቶታልኢነርጂስ የማዲያ ጣብያዎች ኔትዎርክ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ተሳታፊዎች ብቸኛ ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

***አንቀጽ 3፡ የውድድሩ መግለጫ***

በቶታልኢነርጂስ አፍኮን (የአፍሪካ ዋንጫ) ካሜሮን 2021 የእግር ኳስ ውድድር ወቅት "ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ" እንዲሆኑ እድል በመስጠት ቶታልኢነርጂስ ወጣት ደጋፊዎችን ወደ አፍሪካ የእግር ኳስ የልብ ትርታ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡

ውድድሩ በሚጀምርበት ቀን እድሜያቸው ከ13 እስከ 16 ለሚገኙ ልጆች በተለይ ክፍት በሚሆነው የኢንስቴሽን ውድድር ላይ በሚደረገው ተሳትፎ አማካኝነት ለውድድር ብቁ በሆነ ሐገር ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ አዘጋጅ በቶታልኢነርጂስ አፍኮን (የአፍሪካ ዋንጫ) ካሜሮን 2021 ላይ ኳስ አቀባይ እንዲሆን አንድ ልጅ ይመርጣል፡፡

ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ ግጥሚያ ጥሪ የሚደረግ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ምርጫ እየተደረገ ከመሆኑ አንጻር በቀጣይ ጊዜያት ማሳወቂያ ይሰጥበታል፡፡

***አንቀጽ 4፡ ውድድሩ የሚቆይበት ጊዜ***

ውድድሩ ነሐሴ 26/2013 ዓ.ም 2፡00(ጠዋት) በመጀመር መስከረም 20/2014 ዓ.ም 2፡00(ማታ) ይጠናቀቃል፡፡

***አንቀጽ 5፡ የተሳትፎ መስፈርቶች***

5.1. በዚህ ውድድር ላይ ተሳትፎ ለማድረግ አጠቃላይ እነዚህን ሕጎች በምሉዕነት መቀበልን፣ እንዲሁም ተሳትፎ በሚደረግበት ሐገር በስራ ላይ የሚገኙ የስነ-ምግባር ሕጎችን እና ድንጋጌዎችን እና ደንቦችን መቀበልን ይጠይቃል፡፡ በእነዚህ ሕጎች ውስጥ የሰፈሩትን የተሳትፎ መስፈርቶች ሳያከብሩ መቅረት ተሳትፎውን ተቀባይነት ወይም ተፈጻሚነት የሌለው ያደርገዋል፡፡

5.2. በእነዚህ ውድድሮች ላይ የሚደረግ ተሳትፎ ውድድሩ በሚጀመርበት ቀን ሁሉንም ከዚህ በታች የሰፈሩትን ሁኔታዎች በሚያሟሉ ልጆች ላይ ብቻ የሚወሰን ይሆናል (ከዚህ በኋላ "ተሳታፊ" ተብለው የሚታወቁ)፡፡ ተሳታፊዎች የሚከተለውን ማሟላት አለባቸው፡-

- እድሜያቸው ከ 13 እስከ 16 የሆነ
- አፍሪካ ውስጥ የሚኖሩ

- ልጁ/ልጅቷ በሌላ የአፍሪካ ሐገር ውስጥ የሚኖር/የምትኖር ከሆነ ከጥር 1/2014 ዓ.ም እስከ ጥር 29/2014 ዓ.ም የሚካሄደውን የቶታልኢነርጂስ አፍኮን ውድድር ወደምታዘጋጀው ሐገር ወደ ካሜሮን ለመጓዝ እንዲችል/እንድትችል የጸና ወይም አገልግሎቱ ያላበቃ ቪዛ እና ፓስፖርት
- የልጁ/ልጅቷ አሳዳጊ የልጁ/ልጅቷ ተወካይ ለመሆን ስልጣን የተሰጠው መሆን ያለበት ሲሆን ልጁ/ልጅቷ በቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ላይ በሚደረጉ ውድድሮች በአንደኛው ላይ ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ ላይ ተሳታፊ ሆኖ የሚመረጥ/የምትመረጥ ከሆነ አብሮ መጓዝ ይኖርበታል፡፡
- ልጁ/ልጅቷ በሌላ የአፍሪካ ሐገር ውስጥ የሚኖር/የምትኖር ከሆነ ከጥር 1/2014 ዓ.ም እስከ ጥር 29/2014 ዓ.ም የሚካሄደውን የእግር ኳስ ውድድር ወደምታዘጋጀው ሐገር ወደ ካሜሮን ለመጓዝ እንዲችል/እንድትችል የልጁ/ልጅቷ ሕጋዊ አሳዳጊ የቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ውድድር በሚደረግበት ጊዜ የፀና ወይም አገልግሎቱ ያላበቃ ቪዛ እና ፓስፖርት ሊኖረው/ራት ይገባል፡፡
- የልጁ/ልጅቷ ሕጋዊ አሳዳጊ እንደአስፈላጊነቱ የውድድሩን የአስተዳደር መስፈርቶች በተመለከተ ግንኙነት በመፍጠር ማሳወቂያ ሊሰጠው/ጣት እንዲቻል የግል የኢሜይል አድራሻ ሊኖረው/ራት ይገባል፡፡

5.3. የአዘጋጆች ሰራተኞች ወይም ደግሞ በውድድሩ ዝግጅት ላይ በማንኛውም ሐላፊነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያደረጉ በተለይም ለአዘጋጆች የሚሰሩ ሰዎች እንዲሁም የቤተሰቦቻቸው አባላት በውድድሩ ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ሕጋዊነት የላቸውም፡፡

5.4. በሕጎቹ ድንጋጌዎች መሠረት የሚገዙ አካላት ብቻ ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት አዘጋጆቹ የእያንዳንዱን ተሳታፊ ማንነት፣ እድሜ እና የግንኙነት ዝርዝር መረጃን በተመለከተ ሁሉንም አስፈላጊ ማጣሪያዎችን እና ማረጋገጫዎችን የማድረግ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ማንኛውም ያልተሟላ፣ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም ሐሰተኛ መረጃ ወይም ተወዳዳሪው ተሳትፎ እንዲያደርግ የማያስችሉት ማንኛውም መረጃዎች ወደ ተሳትፎ መግባትን እንዲሰረዝ ያደርጋሉ፡፡

5.5. ከአንድ በላይ የኢሜይል አድራሻ በመጠቀም ወጫወት ወይም ለሌላ ሰው በተከፈተ የመጫወቻ አካውንት በመጠቀም መጫወት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ከፍተኛው ለአንድ ልጅ የሚፈቀደው መግቢያ/መመዝገቢያ አንድ ነው(ተመሳሳይ መጠሪያ ስም እና የመጨረሻ ስም፤ ተመሳሳይ የፖስታ አድራሻ)፡፡

5.6. በማንኛውም መንገድ ቢሆን የውድድሩን የአሰራር ሂደቶች በተለይ ውጤቶችን ለመለወጥ ብሎ ማስተካከል ወይም ለማስተካከል መሞከር በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

***አንቀጽ 6፡ በውድድሩ ላይ እንዴት ተሳትፎ ማድረግ ይቻላል?***

በውድድሩ ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ማከናወን አለባቸው፡-

- እርምጃ 1፡ ተሳትፎ በሚደረግበት ወቅት በቶታልኢነርጂስ የማዲያ ጣብያዎች የሚገኘውን የወረቀት ፎርማት የመግቢያ/የመመዝገቢያ ቅጽ መሙላት
- የቅጹ የፊት ክፍል ተሳታፊው/ዋ ለእግር ኳስ ካለው/ካላት ፍቅር ጋር በተያያዘ በህይወቱ/ቷ ያጋጠሙትን/ሟትን ቅጽበቶች ወይም ደግሞ ከሕልሞቹ/ቿ አንደኛውን በስዕል እንዲያሰፍር/እንድታሰፍር እድል የሚሰጥበት ስዕል ለመሳያ የሚውል ባዶ ቦታ አለ፡፡
- የቅጹ የሆነ ክፍል የተሳታፊውን/ዋን እና የሕጋዊ አሳዳጊውን/ዋን ግላዊ መረጃዎች ለማስፈር የሚውል ባዶ ቦታ ያለ ሲሆን፣ ይህ የሚደረገው ለምዝገባው ወይም ለመግቢያው ሕጋዊ ለመሆን ነው፡፡

***ማስታወሻ፡ ቶታል ኢትዮጵያን በተመለከተ፣ ተሳታፊዎች አዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ የቶታል የነዳጅ ማደያዎች ቅጹን መውሰድ (የታተመ ቅጽ) ወይም ደግሞ ከቶታል ኢትዮጵያ ድረ-ገጽ https://totalenergies.et/totalenergies-afcon፣ ዳውንሎድ በማድረግ ፕሪንት/እንዲታተም ማድረግ ይችላሉ፡፡***

- እርምጃ 2፡ በውድድሩ ላይ ያላቸውን ምዝገባ ሕጋዊ ማድረግ፣ ይህ በብቸኝነት ሊደረግ የሚችለው ከሚከተሉት መንገዶች በአንዱ የመመዝገቢያውን ቅጽ በማቅረብ ነው፡-
    - ምዝገባው በተደረገበት ሐገር በሚገኙ የአዘጋጅ የቶታልኢነርጂስ የማደያ ጣብያዎች ለዚሁ አላማ በተቀመጠ ሳጥን ውስጥ ቅጹን ማስገባት
    - ቅጹን ምዝገባው በሚደረግበት ሐገር ለአዘጋጁ የተመዘገበ ቢሮ አድራሻ በፖስታ መላክ

***ማስታወሻ፡ ቶታል ኢትዮጵያን በተመለከተ፣ ተወዳዳሪው/ዋ ቅጹን አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ አራት(4) የተመረጡ የነዳጅ ማደያዎች ማለትም ሜክሲኮ ቶታል፣ ቦሌ መንገድ ቶታል፣ አራት ኪሎ ቶታል እና ላምበረት ቶታል ማቅረብ ወይም ቅጹን በ"1462፣ቶታል ኢትዮጵያ ዋና መ/ቤት፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ" የፖስታ አድራሻ መላክ ይኖርበታል/ባታል፡፡***

በውድድሩ ላይ የሚደረገው ተሳትፎ የሚፈቀደው ከላይ በተጠቀሱት የአሰራር ሂደቶች መሠረት ብቻ ነው፡፡ በሌላ አይነት መንገድ ወይም በሌላ አይነት ዘዴ የሚደረግ ተሳትፎ እውቅና አይኖረውም፡፡

ተሳታፊ የሚያቀርበው/የምታቀርበው መረጃ ሕጋዊ እና እውነተኛ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ይህ ካልሆነ ግን ከውድድሩ ውጪ የሚደረግ/የምትደረግ ከመሆኑ በተጨማሪ ተፈፃሚነት በሚኖርበት ጊዜ አሸናፊነቱን/ቷን ይነጠቃል/ትነጠቃለች፡፡

በተለይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተቀባይነት የሌላቸው ይዘቶች በአፋጣኝ ውድቅ የሚደረጉ ሲሆን እነዚህም ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ፀያፍ ወይም ያልታረሙ፣ ወሲባዊ (ፖርኖግራፊክ)፣ ዘረኝነት፣ ከልጆች ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ልጆችን የሚጎዱ
- ግለሰቦችም ሆኑ ተቋማት የሶስተኛ ወገኖችም ስም ማጥፋት፣ መሳደብ
- ፖለቲካዊ ባህሪ ሲኖራቸው እና/ወይም አዘጋጁ ስስ ወይም መነካት የሌለባቸው (ሴንሴቲቭ) ናቸው ብሎ ሲያምን
- የሶስተኛ ወገኖችን የግል ወይም የምስል መብቶችን መጣስ እና/ወይም ተፈፃሚነት ያላቸው ሕጎችን መጣስ ወይም
- ከመልካም ሞራል እና/ወይም የመንግስት ፖሊሲ ጋር የሚቃረኑ ሲሆኑ

በተመሳሳይ ሁኔታ ተሳታፊዎች በስራ ላይ ባሉ የአእምሮአዊ ንብረት ሕጎች መገዛት ያለባቸው ሲሆን በዚህም መሠረት ምዝገባ በሚደረግበት ወቅት ባለመብቱ ፈቃድ ባልሰጠበት ሁኔታ በማንኛውም አይነት መንገድ ማንኛውንም ይዘቶች (ምልክቶች፣ ጽኁፎች፣ ምስሎች ወይም ማንኛውም አይነት መልዕክቶች) ማባዛት፣ ማሳየት፣ ማሰራጨት ወይም ማከፋፈል አይኖርባቸውም፡፡

በማንኛውም መንገድ ቢሆን በተለይም ውጤችን ለመቀየር ብሎ ወይም ደግሞ በአውቶሜተድ ወይም ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ አሸናፊነት ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር በውድድሩ ሒደት ላይ ማስተካከያ ማድረግ ወይም ማስተካከያ ለማድረግ መሞከር በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ አንድ ተሳታፊ እነዚህን ሕጎች በመጣስ ወይም በማጭበርበር አሸናፊ መሆኑ/ኗ በሚታወቅበት ጊዜ ድርጅቱ ወይም ሶስተኛ ወገኖች በተሳታፊው/ዋ ላይ የሚወስዷቸው ማንኛውም ሕጋዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይህንን መሠል ተሳታፊ ሽልማቱ አይሰጠውም/ጣትም፡፡

***<u>አንቀጽ 7፡ የአመራረጥ እና አሸናፊዎችን የማሳወቂያ የአሰራር ሒደት</u>***

7.1. ውድድሩ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ማለትም በመስከረም 20/2014 ዓ.ም እያንዳንዱ አዘጋጅ ምዝገባዎቹን ማዕከላዊ በማድረግ ሂደቱን ያከናውናል፡፡

7.2. ውድድሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ማለትም ከመስከረም 21/2014 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 5/2014 ዓ.ም የሐገር ውስጥ ሽንገ በእያንዳንዱ አዘጋጅ ዘንድ በማቋቋም ከቀረቡት ሁሉም ስዕሎች ውስጥ በአንቀጽ 3 ላይ የሰፈረውን መስፈርት የሚያሟሉ 5(አምስት) ምርጥ ስዕሎችን ይመርጣሉ፡፡

7.3. በእያንዳንዱ አዘጋጅ ሐገር ውስጥ የተመረጡት 5(አምስት) ተሳታፊዎች መረጃን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ፤ እያንዳንዱ አዘጋጅ ከጥቅምት 5/2014 ዓ.ም በፊት በስልክ ወይም በኢሜይል አማካኝነት ከተሳታፊዎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል።

አዘጋጁ በ5(አምስት) የካላንደር ቀናት ውስጥ ከተሳታፊው/ዋ ዘንድ ምላሽ ካላገኘ በአዘጋጁ ከተመረጡት 5(አምስት) ተሳታፊዎች መካከል ለእርሱ/ሷ የተሰጠው ቦታ በአፋጣኝ ለሌላ ተሳታፊ ይሠጣል።

7.4. በአዘጋጆች የተመረጡት 5(አምስት) ምርጥ ስዕሎች የመጨረሻ ምርጫ እንዲደረግባቸው በሶስተኛው የጥቅምት 2014 ሳምንት ውስጥ ማለትም ከጥቅምት 6/2014 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 12/2014 ዓ.ም ለቶታል ማርኬቲንግ ሰርቪስስ ይላካሉ።

7.5. አዘጋጆቹ የላኩት ስዕሎች ለቶታል ማርኬቲንግ ሰርቪስስ በሚደርስበት ጊዜ ቶታል ማርኬቲንግ ሰርቪስስ ሸንጎ በማቋቋም በአንድ አዘጋጅ አንድ ሰው ይመርጣል። ይህ ምርጫ ከጥቅምት 13/2014 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 19/2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ይከናወናል።

ቶታል ማርኬቲንግ ሰርቪስስ በአንድ አዘጋጅ 1(አንድ) በአጠቃላይ 19 ስዕሎችን ይመርጣል።

7.6. በጥቅምት 19/2014 ዓ.ም የመጨረሻ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ ቶታል ማርኬቲንግ ሰርቪስስ ተሳታፊው/ዋ በቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ላይ ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ በመሆን እንደሚሳተፍ/ምትሳተፍ ለተሳታፊው/ዋ ማሳወቂያ እንዲሰጥ ለእያንዳንዱ አዘጋጅ አሸናፊውን/ዋን ያሳውቃል።

7.7. በመቀጠልም ከጥቅምት 19/2014 ዓ.ም በኋላ ከ7(ሰባት) ባልበለጡ የስራ ቀናት ውስጥ እያንዳንዱ አዘጋጅ በየሃገሩ ለሚገኘው/ለምትገኘው አሸናፊ ማሳወቂያ ይሰጣል። የኢሜይል መልዕክት ወይም የስልክ ጥሪ ከደረሰው በኋላ ከ7(ሰባት) ባልበለጡ የካላንደር ቀናት ውስጥ ማሳወቂያ የተሰጠው አሸናፊ ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ በመሆን በተጋበዘበት/ችበት በቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ግጥሚያዎች ላይ የሚኖረውን/ራትን ተሳትፎ የማረጋገጫውን ቅጽ ለአዘጋጁ በመመለስ ማረጋገጥ ይኖርበታል/ባታል።

7.8. አሸናፊው/ዋ ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ እና የጊዜ ገደብ በሃገር ውስጥ ለሚገኘው አዘጋጅ ምላሽ ሳይሰጥ/ሳትሰጥ ቢቀር፤ ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ በመሆን የተሰጠውን/ጣትን ቦታ ይነጠቃል/ትነጠቃለች።

ጥርጣሬን ለማስወገድ ሲባል፤ ያልተመረጠ/ች ተሳታፊ ማሳወቂያ እንደማይሰጠው/ጣት መግለጽ ያስፈልጋል።

## *አንቀጽ 8፡ የሽልማት አሰጣጥ እና አጠቃቀም*

### *8.1. የሽልማት አሰጣጥ እና አጠቃቀም*

እያንዳንዱ ተሳታፊ ሐገሩ/ሯ ውስጥ ከሚገኝ አዘጋጅ ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ በመሆን በቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ላይ ተሳትፎ እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥ ሰነድ በፖስታ ቤት አድራሻው/ዋ ይደርሰዋል/ሳታል።

በጥቅምት 19/2014 ዓ.ም እና ታህሳስ 28/2014 ዓ.ም መካከል ባሉት ጊዜያት ኩነቱን በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ለመስጠት እና በቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ጨዋታዎች ላይ የሚገኙባቸውን ቀናቶች ለማሳወቅ አዘጋጁ ተሳትፎአቸው ከተረጋገጠላቸው አሸናፊዎች ሕጋዊ አሳዳጊዎች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል።

### *8.2. የሽልማቱን አጠቃቀም በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ*

ማንኛውም አሸናፊ በማንኛውም አይነት ሁኔታ የተሰጠውን/ጣትን ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ ሽልማት በተመለከተ መከራከር አይኖርበትም/ባትም። እያንዳንዱ የሚሰጥ ሽልማት ጥብቅ በሆነ መንገድ ግላዊ ሲሆን ለሌላ ሶስተኛ ወገን አይተላለፍም ወይም አይሸጥም። ከዚህ በተጨማሪ አዘጋጁ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ወይም በአይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ማንኛውንም የጥሬ ገንዘብ ተመላሽ ወይም ለውጥ አያደርግም ወይም ተመጣጣኝነት ያለውን ዋጋ አይልክም።

## *አንቀጽ 9፡ ማስታወቂያ እና አሸናፊዎችን ማስተዋወቅ*

በተለይ ተቃውሞ የሚኖረው/ራት ካልሆነ በስተቀር ልጁ/ጇ ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ እንዲሆን በብቸኝነት የፈቀደ/ች የአሸናፊው/ዋ ተሳታፊ ሕጋዊ አሳዳጊ በሃገር ውስጥ የሚገኘው አዘጋጅ የአሸናፊውን/ዋን የመጠሪያ እና የመጨረሻ ስም እንዲሁም አሸናፊው/ዋ የሚኖርበትን/የምትኖርበትን ከተማ በማንኛውም መንገድ በተለይ በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ መንገድ ከውድድሩ ጋር በተያያዘ ተሳትፎው/ተሳትፎዋ ማሳወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ከዚህ ቀን በኋላ 6(ስድስት) ወራት እስከሚያበቃ ድረስ ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ ከመሆን ውጭ ሌላ ምንም አይነት ክፍያ ወይም ጥቅማጥቅም የመጠየቅ መብት ሳይኖረው በአፍሪካ፣ ማዳጋስካር፣ ማዮቴ፣ ሪዩኒየን ደሴት፣ ሞሪሺየስ + ደሴቶች እንዲሁም ሜንላንድ ፈረንሳይ ውስጥ ማስታወቂያ እና የማስታወቂያ ስራዎችን ለመስራት አላማ እንዲያውለው ፈቃድ ይሰጣል/ትሰጣለች።

የአሸናፊው/ዋሕጋዊ ተወካይ ይህንን የሚቃወም ከሆነ በሚከተለው አድራሻ በሚላክ ደብዳቤ ይህንኑ መጥቀስ ይኖርበታል/ባታል፡ Ballkids.Ethiopia@totalenergies.et

***አንቀጽ 10፡ ሕጎቹን ስለማግኘት***

ውድድሩ በሚከናወንበት ጊዜ ውስጥ ሕጎቹን ከሚከተለው ሊንክ ማየት፣ ዳውንሎድ ማድረግ እና በኦንላይን ፕሪንት ማድረግ ይቻላል፡ https://totalenergies.et/totalenergies-afcon

በመደበኛ ወረቀት ለውድድሩ አድራሻ የጽሁፍ ጥያቄ ለሚያቀርብ እና ውድድሩ ከመጠናቀቁ በፊት ከ10(አስር) ባላነሱ የስራ ቀናት ውስጥ ሙሉ የመገኛ አድራሻውን (የመጠሪያ እና የመጨረሻ ስም፣ የፖስታ አድራሻ) ለሚያቀርብ ማንኛውም ሰው (በፖስታ ቤት ምልክት ማስረጃነት) ሕጎቹ በፖስታ ቤት አማካኝነት ሊላኩለት ይችላሉ፡፡

በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ማንኛውም ያልተሟላ ወይም ግልጽ ያልሆነ ጥያቄ ወይም ከላይ ከተጠቀሰው አድራሻ በተፃራሪ በሌላ አድራሻ የተላከ ጥያቄ ወይም ከላይ የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካበቃ በኋላ የተላከ ጥያቄ (በፖስታ ቤት ምልክት ማስረጃነት) ተቀባይነት እንደሌለው ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ውድድሩ በሚራዘምበት ወይም በሚተላለፍበት ጊዜ፤ ሕጎቹን ለማግኘት ጥያቄ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ በዚሁ መሠረት የሚራዘም ይሆናል፡፡

***አንቀጽ 11፡ ለውጦች፣ እገዳ እና መሰረዝ***

ከአቅም በላይ ወይም ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ውድድሩ ቢሰረዝ፣ ቢተላለፍ፣ ቢታገድ፣ ቢሻሻል፣ ወይም ጊዜው እንዲያጥር ቢደረግ አዘጋጁ ተጠያቂነት አይኖርበትም፡፡ በማንኛውም አይነት ሁኔታ ቢሆን አዘጋጁ የተሳትፎውን ጊዜ የማራዘም እና ማሳወቂያ የተሰጠበትን ማንኛውንም ቀን እና/ወይም ሰዓት የማስተላለፍ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ውድድሩ በሚደረግበት ወቅት የአዘጋጁ ሕጎቹን የመቀየር መብት የተጠበቀ ነው፡፡ ማንኛውም በ፡https://totalenergies.et/totalenergies-afcon ላይ የተገለፁ እና በቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ የተመዘገቡ የታተሙ የሕጎቹ ማሻሻያዎች ይፋ ከተደረጉ በኋላ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ወይም የሚፀኑ ይሆናል፡፡

ለውጡ ከፀናበት ጊዜ በኋላ ባለው ቀን በቀላሉ ተሳትፎ በማድረግ እነዚህን ለውጦች እንደተቀበሉ ለማሳየት የሚችሉ ሲሆን፤ አዘጋጁ በሕጎቹ ላይ የሚያደርጋቸውን ማንኛውንም ለውጦች በተመለከተ ማንኛውንም የክፍያ ጥያቄ ወይም የመቃወም መብታቸውን ይለቃሉ፡፡

በውድድሩ ላይ ተሳትፎ ከሚያደርጉ ተሳታፊዎች ጋር በተያያዘ ማጭበርበር የተከሰተ ከሆነ አዘጋጁ ሁሉንም ወይም ማንኛውንም የውድድሩን ክፍሎች ሊሰርዝ ይችላል፡፡

## *አንቀጽ 12፡ የተሳታፊዎችን የግል መረጃ ስለመጠቀም*

### *12.1. የመረጃ አሰባሰብ*

በውድድር ላይ ተሳትፎ ከማድረግ ጋር በተገናኘ ተሳታፊዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች በአዘጋጁ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ለውድድር ምዝገባ በሚደረግበት ወቅት የሚሰበሰብ የግል መረጃ (ከዚህ በኋላ "የግል መረጃ" ተብሎ የሚታወቅ) ውድድሩን ለማካሄድ እና ለተሳታፊዎች ደረጃ ለመስጠት አላማ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ከዚሀ በተጨማሪ በተሳታፊዎች ፈቃድ ላይ በመመስረት አዘጋጁ የግል መረጃውን ለሽያጭ አላማዎች (መላላኮች ወይም የሽያጭ አቅርቦቶች) ጥቅም ላይ ሊያውላቸው ይችላል፡፡ በእያንዳንዱ መልዕክት ላይ የተዘረዘሩትን ዘዴዎች በመጠቀም እያንዳንዱ ተሳታፊ እነዚህን የግንኙነት ወይም የሽያጭ አቅርቦቶች የመቀበል ወይም እንዲደርሰው የማድረግ ፈቃዱን ሊያነሳ ይችላል፡፡ አዘጋጁ በተመዘገበበት ሐገር ሕጎች መሠረት የግል መረጃን በመሰብሰብ ጥቅም ላይ ያውላል፡፡

### *12.2. መረጃ ተቀባዮች*

በብቸኝነት ከድርጅቱ አላማዎች ጋር በተገናኘ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ስራ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ እንዲሁም ውድድሩ በአግባቡ እንዲከናወን ለማድረግ አዘጋጁ ከተሳታፊዎች የተሰበሰበውን መረጃ ለተወሰኑ የአዘጋጁ የስራ ክፍሎች እንዲሁም ለአይቲ አገልግሎት አቅራቢዎች እና እንደ አዘጋጁ በመሆን ለሚሰሩ ንዑስ ስራ ተቋራጮች ሊያሳውቅ ይችላል፡፡

ቅጹ በቀረበበት ሐገር ውስጥ በስራ ላይ ባሉ ሕጎች እና ደንቦች መሠረት ከፍትህ አካላት ወይም በሕጉ ከፈተቀደላቸው ማንኛውም የአስተዳደር ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ዘንድ እነዚህ የግል መረጃዎች እንዲቀርቡ የሚጠይቅ ጥያቄ ሲደርሰው አዘጋጁ የግል መረጃዎችን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

### *12.3. መረጃን ማስተላለፍ*

ማንኛውም ከአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ አካባቢ (ዩሮፐያን ኢኮኖሚክ ኤርያ) ውጪ ለሚገኙ ሶስተኛ ሃገራት የሚደረግ ማንኛውም የግል መረጃ ማስተላለፍ ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጎች እና በበቂ ሁኔታ መረጃው እንደሚጠበቅ በሚያረጋግጥ መንገድ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ከአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ አካበቢ (ዩሮፐያን ኢኮኖሚክ ኤርያ) ለሚገኙ እና ከአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ አካባቢ (ዩሮፐያን ኢኮኖሚክ ኤርያ) ውጪ ለተመሰረቱ የቶታል ግሩፕ ተቋማት የሚተላለፉ የግል መረጃዎች ጥበቃን በቂ መሆኑን ለማረጋገጥ ገዢ የኮርፖሬት ሕጎች (ቢሲአር) በስራ ላይ ውሏል፡፡ የእኛን ቢሲአር

በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎን https://www.fr.total.com/version-resumee-des-binding-corporate-rules-de-total ክሊክ ያድርጉ።

በቢሲአር ስር ላልተሸፈኑ እና ከአውሮፓ ኢኮኖሚያዊ አካባቢ (ዩሮፐያን ኢኮኖሚክ ኤርያ) ውጪ ለሆኑ ሃገራት የሚተላለፉ የግል መረጃዎችን በተመለከተ የግል መረጃዎቹ በቂ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ለማረጋገጥ ሌላ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። በቂ ጥበቃ እንደሚኖር ለማረጋገጥ የሚወሰዱ ሌላ እርምጃዎችን በተመለከተ መረጃ ከፈለጉ እባክዎን ከታች በሰፈረው አድራሻ ይፃፉልን።

### 12.4. የግል መረጃ ደህንነት እና ምስጢራዊነት

የግል መረጃ ደህንነት እና ምስጢራዊነትን ለማረጋገጥ በተለይም የግል መረጃ እንዳይቀየር ወይም እንዳይበላሽ ለመከላከል እና ያልተፈቀደላቸው ሶስተኛ ወገኖች የግል መረጃውን እንዳያገኙ ለማድረግ ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጎች እና ደንቦች መሠረት አዘጋጁ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች ተግባራዊ አድርጓል።

### 12.5. የግል መረጃን ስለመያዝ

አግባብነት ያለው አሰራር እንደሚኖር ለማረጋገጥ አጠቃላይ ውድድሩ በሚከናወንባቸው ጊዜያት ውስጥ ማለትም እስከ ጥር 29/2014 ዓ.ም አዘጋጁ የግል መረጃዎችን ይይዛል። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በሕጉ ለሚጠቀስ ተፈፃሚነት ላለው ጊዜ የግል መረጃዎች በጊዜያዊ ማሕደሮች ሊያዙ ይችላሉ።

### 12.6. የተሳታፊዎች መብት

ተፈፃሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት፤ ተሳታፊዎች የግል መረጃቸውን የማግኘት፣ የማሻሻል እና እንዲሰረዙ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሲሆን የሚደረጉትም ሂደቶች የተገደቡ እንዲሆኑ ሊጠይቁ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ተሳታፊዎች የመረጃ ቅይይርን በተመለከተ መብት ያላቸው ሲሆን የሽያጭ አላማዎችን ጨምሮ አጠቃቀሞችን ሊቃወሙ ይችላሉ። በእነዚህ ሕጋዊ መሠረቶች ላይ ሒደቶች የሚፈፀሙ ከሆነ ተሳታፊዎች በማንኛውም ጊዜ የሰጡትን ፈቃድ ሊያነሱ ይችላሉ።

መብቶቻቸውን ለመጠቀም እና/ወይም የግል መረጃቸው ላይ የሚፈፀመውን ሒደት በተመለከተ መረጃ መጠየቅን በተመለከተ፤ ተሳታፊዎች በአዘጋጁ ሳይት በግል መረጃ ፖሊሲዎች ላይ በሰፈረው አድራሻ ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብ ይችላሉ።

ከአዘጋጁ ጋር ግንኙነት ከፈጠሩ በኋላ ተሳታፊዎች መብታችን አልተከበረም ብለው ካሰቡ ስልጣኑ ላለው ተቆጣጣሪ አካል ቅሬታቸውን ማቅረብ ይችላሉ።

***አንቀጽ 13፡ አእምሮአዊ ንብረት - የምስል መብቶች***

13.1. በእነዚህ ሕጎች ውስጥ እንዲሁም ከውድድሩ ጋር በተገናኘ በሚደረጉ ማንኛውም የግንኙነት ማቴሪያሎች ላይ የተጠቀሱ ሁሉም ስሞች ወይም የንግድ ምልክቶች የፈጠሯቸው ወይም ያስመዘገቧቸው ወገኖች ብቸኛ ንብረቶች ናቸው፡፡

13.2. ምስሎች እና ቪዲዮዎች፣ በወካይነት ጥቅም ላይ የዋሉ ነገሮች፣ የተጠቀሱ የንግድ ምልክቶች እና የንግድ ስሞች፣ የግራፊክስ እና የኮምፒዩተር ኤለመንቶች እና የመረጃ ቋቶች የእያንዳንዱ ባለቤቶች ብቸኛ ንብረቶች ሲሆኑ በቅድሚያ እነዚህ ወገኖች የጽሁፍ ፈቃድ ካልሰጡ በስተቀር ተቆንስለው አይወሰዱም፣ አይባዙም ወይም ጥቅም ላይ አይውሉም፡፡ በዚህ ላይ ጥሰት የሚፈጽሙ በፍትሃብሄር እና/ወይም የወንጀል መቀጫ ይጠየቃሉ፡፡

13.3. በቅድሚያ አዘጋጁ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ግንኙነት የተደረገባቸውን ኤለመንቶች (ክፍሎች) በተሳታፊዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በድጋሚ ማባዛት፣ ማሳየት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

13.4. ማንኛውም በውድድሩ ላይ ያሉ ገጸ-ባህሪዎች ወይም ኤለመንቶች ከሌላ ልብወለዳዊ ገፀባህሪያት ወይም በአሁኑ ወቅት ከሚገኙ ሌላ ኤለመንቶች ጋር ተመሳሳይነት ቢኖራቸው ይህ አጋጣሚ ሲሆን፤ በአዘጋጁ ወይም በአገልግሎት አቅራቢዎቹ ላይ ተጠያቂነት አያስከትሉም፡፡

13.5. ውድድሩ ከሚጀመርበት ከነሀሴ 26/2013 ዓ.ም ጀምሮ የቶታልኢነርጂስ አፍኮን ውድድር እስከሚጠናቀቅበት እስከ ጥር 29/2014 ዓ.ም ድረስ አዘጋጁ የወደፊት ኳስ አቀባይ ልጅ በቶታልኢነርጂስ መኖርን የሚጠይቅ በሚሆንበት ጊዜ የቪዲዮ ቀረፃ ሊያከናውን ይችላል፡፡

ተሳትፎውን/ዋን በማረጋገጥ የተሳታፊው/ዋ ሕጋዊ አሳዳጊ አዘጋጁ ከሚያከናውናቸው የቪዲዮ ቀረፃዎች/ፎቶግራፎች ጋር በተገናኘ የተሳታፊውን/ዋን የምስል መብት የመጠቀም ፈቃድ ይሰጣል፡፡

***አንቀጽ 14፡ ተጠያቂነት***

14.1. ተሳታፊው/ዋ ወደ ውድድሩ በመግባቱ ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም አይነት ጉዳት (የግል ጉዳት፣ አካላዊ ጉዳት፣ የንብረት ጉዳት፣ የገንዘብ ኪሳራ ወዘተ) አዘጋጁ ተጠያቂነት አይኖርበትም፡፡ ተሳታፊው/ዋ ወደ ውድድሩ ሲገባ/ስትገባ ይህንን ሁኔታ ተቀብሎ/ላ ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ መሠረት ምንም አይነት ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

14.2. የአሸናፊዎችን ጤንነት ለመጠበቅ አዘጋጁ አስፈላጊውን የጤና ፕሮቶኮል ተግባራዊ ያደርጋል (ከመድረሳቸው በፊት የሚቀርብ የኮቪድ ምርመራ፣ በቦታ ላይ የሚደረጉ ምርመራዎች፣ የእጅ ማጽጃ ጄሎችን/ሳኒታይዘር/ እና ሰርጂካል ማስኮችን ማቅረብ፣ የኮቨድ-19 መስፋፋትን ለመከላከል ስለ ርቀት አጠባበቅ ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት)፡፡ አዘጋጁ ኳስ አቀባይ ልጆች

በቶታልኢነርጂስ ተሳትፎ የሚያደርግበት ቶታልኢነርጂስ አፍኮን ካሜሮን 2021 ውድድሮች በሚደረጉበት ወቅት ለጤና አጠባበቅ ሁኔታዎች ምክንያት የጤንነት ሁኔታው የተሳታፊዎችን ተሳትፎ የማይፈቅድ በሚሆንበት ጊዜ አዘጋጁ ውድድሩን ሙሉ በሙሉ ወይም ማንኛውንም የውድድሩን ክፍሎች ሊሰርዝ ይችላል።

14.3. በማንኛውም ሁኔታ የማጭበርበር ተግባራት በሚከሰቱበት ጊዜ አዘጋጁ ውድድሩን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሰርዝ ይችላል። ይህንን መሠል ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ አዘጋጁ የማጭበርበር ድርጊት ለፈጸሙት ሽልማቱን ያለመስጠት እና/ወይም ስልጣኑ በተሰጠው ፍርድ ቤት በድርጊቱ ፈፃሚዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው።

14.4. አዘጋጁ በሃገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ተሳታፊ የቶታልኢነርጂስ ኔትዎርክ የነዳጅ ማደያዎች አክሰስ ለማግኘት እንዲችሉ የተቻለውን ጥረት የሚያደርግ ሲሆን ይሁን እንጂ ይህንን በተመለከተ ግዴታ አይኖርበት። በተለይ በቴክኒካዊ ምክንያቶች ወይም ደግሞ የማሻሻያ እና ጥገና ስራዎችን ለመስራት አዘጋጁ በማንኛውም ጊዜ ውድድሩን ሊያቋርጥ ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን አዘጋጁ ለዚህ መሰል ማቋረጥ እና ተከታይ ውጤቶች ተጠያቂ ተደርጎ አይወሰድም።

14.5. በቅጹ ላይ የሰፈረው መረጃ የማይታይ መሆኑን ጨምሮ ተጠያቂነት በማያስወስድበት መልኩ የተሳታፊው/ዋ ምዝገባ ጋር የተያያዙ ግላዊ መረጃዎች በማንኛውም ምክንያት ሳይደርሱት ቢቀሩ አዘጋጁ ተጠያቂነት አይኖርበትም።

14.6. በማንኛውም አይነት ሁኔታ ቢሆን አዘጋጁ የተሳታፊው የግል መረጃን መጥፋትን ወይም መበላሸትን በተመለከተ ተጠያቂነት አይኖርበትም።

***<u>አንቀጽ 15፡ ያለማካተት መብት</u>***

አዘጋጁ በአፋጣኝ እና ያለ ምንም ማሳወቂያ ማንኛውንም በሕጎቹ መሠረት የማይገዛን ተሳታፊ እንዳይካተት ሊያደርግ እንዲሁም የተጠቀሰው ተሳታፊ የሚኖረውን ማንኛውንም አሸናፊነት በአፋጣኝ ሊሰርዝ ይችላል።:

ከዚህ በተጨማሪ በአፋጣኝ እና ያለ ምንም ማሳወቂያ አዘጋጁ የተሳታፊውን ማንነትን እና እድሜን በተመለከተ ግልጽ ስህተቶች የያዙ የውድድር ምዝገባዎችን ሊሰርዝ ይችላል።

ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውንም ሽልማቱን ለማሸነፍ ብሎ/ላ ፍትሃዊ እና/ወይም ባልተለመደ ሁኔታ ዘዴዎችን የተጠቀመ/ች ወይም የፈጠረ/ች ተሳታፊን የውድድር ምዝገባን አዘጋጁ ለመሰረዝ እንደሚችል ተሳታፊው/ዋ ይገነዘባሉ። ይህንን መሠል ስረዛ በማንኛውም ጊዜ እና ያለ ምንም ማሳወቂያ ሊደረግ ይችላል። ይህንን በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም።

***አንቀጽ 16፡ የማስረጃ ስምምነት***

አዘጋጁ በተለይ ለማረጋገጫነት ማንኛውንም እውነታ ወይም የተፈፀመ ግድፈት ወይም ማንኛውም ፕሮግራም፣ ዳታ፣ ፋይል፣ ተመዝግቦ የተያዘ፣ የኦፕሬሽን ወይም ሌላ ኤለመንት (ክትትሎችን እና ሌላ ሪፖርቶችን የመሳሰሉ)፣ የኮምፒዩተር ወይም የኤሌክትሮኒክ ፎርማቶችን ወይም ሚዲያዎችን፣ የተዘጋጁ፣ የተሰበሰቡ ወይም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተከማቹ /በተለይ በመረጃ ስርዓቶች ውስጥ/ ሊጠቀም ይችላል።

በዚህም መሠረት እነዚህ ኤለመንቶች በማንኛውም የሕግ ሒደት ወይም ክስ በአዘጋጁ በማስረጃነት ሊቀርቡ የሚችሉ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ እና በተመሳሳይ መንገድ ሌላ የሚቀርቡ፣ የተሰበሰቡ ወይም በጽኑፍ የተቀመጡ ሰነዶች በሚኖራቸው ተቀባይነት ሁኔታ ተቀባይነት፣ ሕጋዊነት እና ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

***አንቀጽ 17፡ ቅሬታዎች***

የሕጎቹን አፈጻጸም ወይም አተረጓጎም በተመለከተ ማንኛውም ቅሬታዎች ቢኖሩ በጽኑፍ በሚከተለው የኢሜይል አድራሻ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡- Ballkids.Ethiopia@totalenergies.et

ይሁን እንጂ፤ አዘጋጁ አግባብነት የላቸውም ብሎ ለሚያምንባቸው ቅሬታዎች ምላሽ የመስጠት መብቱ የተጠበቀ ነው።

***አንቀጽ 18፡ ስነ-ምግባር***

18.1. አዘጋጁ ሙስናን፣ ማጭበርበርን እና የሕጋዊ ፉክክር ህጎች ጥሰቶችን በተመለከተ ባሉ ሕጎች የሚገዛ ሲሆን እያንዳንዱ ተሳታፊ ተመሳሳይ ቁርጠኝነት እንዲሳይ/እንድታሳይ ይጠብቃል።

18.2. ከዚህ በተጨማሪ፤ እያንዳንዱ ተሳታፊ በውድድሩ ላይ ተሳትፎ በሚያደርግበት/በምታደርግበት ጊዜ በተለይ በቤተሰብ፣ በስራ ወይም በሌላ ግንኙነቶች ምክንያት የሚኖሩ እና ተሳትፎው/ዋ ላይ ጥርጣሬ ሊያስነሱ የሚችሉ የጥቅም ግጭቶችን ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል/ባታል።

***አንቀጽ 19፡ ገለልተኛ ወገኖች***

በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን በጨዋታዎቹ ላይ መመዝገብ እና ተሳትፎ ማድረግ በአዘጋጁ እና በተሳታፊዎች መካከል የስራ ግንኙነት የሚፈጥር አይሆንም።

***አንቀጽ 20፡ ገዢ ሕግ - ስልጣን***

20.1. የሕጎች መርሆዎች ግጭትን ለማስወገድ እነዚህ ሕጎች አዘጋጁ በተመዘገበበት በተሳታፊ ሐገር ሕጎች በተለይ የሚገዙ ይሆናል፡፡

20.2. ማንኛውም ከውድድሩ ጋር በተያያዘ የሚፈጠር ያለመግባባት እንደ ያለመግባባቱ ሁኔታ በአዝል 2 ላይ በተጠቀሰው መሠረት አዘጋጁ በተመዘገበበት ከተማ ለሚገኝ ስልጣኑ ለተሰጠው ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

***አንቀጽ 21፡ አጠቃላይ ሰነድ - ተፈፃሚ ያለመደረግ***

በሕጎች ወይም ደንቦች ለውጥ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ምክንያት ማንኛውም የእነዚህ ሕጎች ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይደረግ በሚሆንበት ጊዜ የሚኖሩ ግዴታዎች እና በሌላ የሕጎቹ ድንጋጌዎች ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አይፈጠርም፡፡

***አንቀጽ 22፡ የሕጎች ምዝገባ***

እነዚህ ሕጎች መስሪያ ቤቱ በደብረዘይት መንገድ-ሙለጌ ሕንጻ (7ኛ ፎቅ) በሚገኘው ቶታል ኢትዮጵያ አ.ማ የሚገኙ ሲሆን በBallkids.Ethiopia@totalenergies.et አማካኝነት የጽሁፍ ጥያቄ ለሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ያለ ምንም ክፍያ ይላካሉ፡፡

*<u>አባሪ 1፡ በቶታልኢነርጂስ አፍኮን (አፍሪካ ካፕ ኦፍ ኔሽንስ) ካሜሮን 2021 ላይ የሚሳተፉ ሐገራት</u>*

**ማስታወሻ፡** የሀገር ውስጥ የቶታልኢነርጂስ ተባባሪ የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት በቶታልኢነርጂስ አፍኮን (አፍሪካ ካፕ ኦፍ ኔሽንስ) ካሜሮን 2021 ላይ ተሳትፎ በሚያደርጉ በተለይ የተጠቀሱ ሃገራት ውስጥ ኳስ አቀባይ ልጆች በቶታልኢነርጂስ የተሰኘው ውድድር አይከናወንም፡፡ እነዚህም ሃገራት ኬፕቬርዲ ፣ ኮሞሮስ፣ ጋምቢያ፣ ሱዳን፣ ቤኒን እና ሴራሊዮን ናቸው፡፡

1. አልጄሪያ
2. ቡርኪናፋሶ
3. ካሜሮን
4. ኬፕቬርዲ (የሃገር ውስጥ የቶታልኢነርጂስ ተባባሪ የለም)
5. ኮሞሮስ (የሃገር ውስጥ የቶታልኢነርጂስ ተባባሪ የለም)
6. አይቮሪኮስት
7. ግብጽ
8. ኢትዮጵያ
9. ጋቦን
10. ጋምቢያ (የሃገር ውስጥ የቶታልኢነርጂስ ተባባሪ የለም)
11. ጋና
12. ጊኒ - ቢሳው
13. ጊኒ ኮናክሪ
14. ኢኳቶሪያል ጊኒ
15. ማላዊ
16. ማሊ
17. ሞሪታኒያ
18. ሞሮኮ
19. ናይጄሪያ
20. ሴኔጋል
21. ሱዳን (የሃገር ውስጥ የቶታልኢነርጂስ ተባባሪ የለም)
22. ቱኒዚያ
23. ዚምባብዌ
24. ቤኒን/ሴራሊዮን (የሃገር ውስጥ የቶታልኢነርጂስ ተባባሪ የለም)

***<u>እዝል 2፡ የአዘጋጆች ዝርዝር (ያልተሟላ)</u>***

| |
|---|
| • ቶታል ሊብሪፊያንትስ አልጄሪያ ኤስፒኤ፧ የጆይንት ስቶክ ኩባንያ (ሶሳይቴ ፓር አክሽንስ) የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 20፧ ፊንጃ-ኤል ቢያር፧ 16023 አልጀርስ፧ በንግድ ምዝገባ በቁ 096022231 ቢ.03 የተመዘገበ<br>• ቶታል ማርኬቲንግ ኤንድ ሰርቪስስ አንጎላ ኤስ.ኤ፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፧ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ራይና ጂንጋ መንገድ ቁ.128፧ ኢንትሬፒሶ - ቲቲኤ1 ሉዋንዳ፧ በንግድ ምዝገባ በቁ 7.164-19/191028 የተመዘገበ |
| • ቶታል ቡርኪና፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ ፓር አክሽንስ) ፧ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ቢፒ21 ዋጋዱጉ 01፧1080 ክዋሜ ንኩሩማህ ጎዳና ፧ ዋጋዱጉ ውስጥ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ ኦዩኤ 1999 ቢ. 779 የተመዘገበ |
| • ቶታል ካሜሮን ኤስኤ፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ ፓር አክሽንስ)፧ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያለው እና የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 589 ቡልቫርድ ደ ላ ሊበርቴ፧ ዱዋላ -አክዋ፧ በንግድ እና የግል ንብረት ብድር ምዝገባ (አርሲሲኤም በቁ አርሲ/ዲኤልኤ/1975/ቢ/5138፧ ዱዋላ፧ ቦይቴ ፖስታል 4048 ዱዋላ፧ ካሜሮን የተመዘገበ) |
| • ቶታል ሴንትራፍሪኬ፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ) የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ቢፒ 3295፧ ባንጉዊ፧ በንግድ እና የግል ንብረት ብድር ምዝገባ (አርሲሲኤም በቁ ሲኤቢጂ2019ኤም1328 የተመዘገበ)<br>• ቶታል ኮንጎ ኤስኤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ) የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ሩ ደ ላ ኮርኒቼ፧ ዲፒ 1037፧ብራዛቪል ውስጥ በንግድ ምዝገባ በአርሲሲኤም ቁ 01-ቢ-3025-ኤንአይዩ ኤም 2005110000197159 የተመዘገበ |
| • ቶታል ኮት ዲቩዋር፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ) የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ኢሜዉብል ሪቭ ጋውቼ፧ 100 ሩ ደስ ብራሴዉርስ-ዞን 3 01-ቢፒ 336 አቢጃን 01፧ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ ሲአይ-ኤቢጄ-1976-ቢ-17247 የተመዘገበ |
| • ቶታል ኢጂብት፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ፧ በግብጽ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ እና የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 20/254 ዴግላ መንገድ-ማዲ፧ ካይሮ፧ በደቡብ ካይሮ የንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ 8724 የተመዘገበ<br>• ቶታል ኤርትራ፧ የአክስዮን ማሕበር፧ በኤርትራ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፧ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 213 ሰማዕታት ጎዳና፣ መ.ሳ.ቁ 871 አስመራ በንግድ እና ኢንዱስትሪ ምዝገባ በቁ ኤኤስአር00002779 የተመዘገበ |

| |
|---|
| • ቶታል ኢትዮጵያ፤ የአክስዮን ማሕበር፤ በኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ቂርቆስ ክ/ከተማ ፣ ወረዳ 03፣ የቤት ቁጥር 069 እና የኢንቮይሲንግ አድራሻው ደብረዘይት መንገድ-ሙለጌ ሕንጻ (7ኛ ፎቅ) የሚገኝ፤ መ.ሳ.ቁ 1462 አዲስ አበባ፤ በኢትዮጵያ ቁ 020/2/4252/99 የተመዘገበ |
| • ቶታል ጊኒ ኢኳቶርያል፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ካሌ ኬንያ፤ ቢፒ 647 ማላቦ፤ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ 255/52 የተመዘገበ |
| • ቶታል ማርኬቲንግ ጋቦን፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ)፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ቡልቫርድ ደ ለ ኢንዲፔንዳንስ፤ ቢፒ 540፤ ሊበርቪል፤ በንግድ እና የግል ንብረት ብድር ምዝገባ (አርሲሲኤም) በቁ.2004 ቢ 03471 የተመዘገበ |
| • ቶታል ፔትሮሊየም ጋና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር፤ በጋና ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 25 ላይቤርያ መንገድ፤ አክራ፤ በቁ476 የተመዘገበ |
| • ቶታል ጊኒ ኤስኤ ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ)፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያለው እና የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ኮሊያህ ኬኤም4-ሩት ዱ ኒጀር፤ ኮናክሪ፤ ኮናክሪ ውስጥ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ ጂሲኬአርዋይ/0609ኤ/2003 ካለም የተመዘገበ |
| • ቶታል ኬንያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር ፤ በኬንያ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ሬጋል ፕላዛ፤ ሊሙሩ መንገድ፤ መ.ሳ.ቁ 30736-00100፤ ናይሮቢ፤ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ 3269 የተመዘገበ |
| • ቶታል ማዳጋስካራ ኤስኤ ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ)፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ኢሜዉብል ፊታራትራ-ሩ ራቮኒናሂትሪኒያሪቮ አንኮሮንድራኖ፤ አንታናናሪቮ፤ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ 3819/1999 ዲ 00761 የተመዘገበ |
| • ቶታል ማላዊ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፤ በማላዊ ሕጎች መሰረት የተቋቋመ፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ኦፍ ማሳዎኮ ቺፔምቤሬ ሃይዌይ፤ መ.ሳ.ቁ 5125 ማሴሌማ፤ ሊምቤ፤ በምዝገባ ቁ ሲኦዋይ 757 የተመዘገበ |
| • ቶታል ማሊ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ)፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ቲምቡክቱ ጎዳና፤ ዳከሎ ባማኮ-ቢፒ 13፤በአርሲሲኤም ቁ ኤምኤ.ቢኬኦ.2004.ቢ.4093 የተመዘገበ |
| • ቶታል ማሮክ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ)፤ በሞሮኮ ሕጎች መሰረት የተቋቋመ፤ በካዛብላንካ የንግድ ምዝገባ በቁ 39 የተመዘገበ እና የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 146 ቦልቫርድ ዜርክቱኒ 20 000፤ ካዛብላንካ፤ ሞሮኮ |
| • ቶታል ሞሪሺየስ፤ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፤ በሞሪሺየስ ሕጎች መሰረት የተቋቋመ፤ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ቻውሲ ትሮሜሊን 11609-መ.ሳ.ቁ 1202 ፖርት ሉዊስ፤ በንግድ ምዝገባ በቁ ሲ07000961 የተመዘገበ |

- ቶታል ሞዛምቢክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ በሞዛምቢክ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ አቬኔዳ ሶሲዬዳድ ጂኦግራፊያ፣ ቁ83፣ 5º አንዳር ማፑቶ፣ በምዝገባ ቁ 400007292 የተመዘገበ
- ቶታል ናይጀሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ በናይጀሪያ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 4 ቸርችጌት መንገድ፣ ቪክቶሪያ አይላንድ፣ ሌጎስ፣ በምዝገባ ቁ 1 369 የተመዘገበ
- ቶታል አርዲሲኤስኤ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር(ሶሳይቴ አኖኒሜ)፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ያሉት እና የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 24፣ካዴኮ ጎዳና ኪንሻሳ፣ አርሲሲኤም ውስጥ በቁ ሲዲ/ኬአይኤን/አርሲሲኤም/14-ቢ-3571 የተመዘገበ
- ቶታል ሴኔጋል ኤስኤ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር (ሶሳይቱ አኖኒሜ)፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ሩት ደ ለ ኤሮፖርት፣ ሱር ላ ስቴሽን ቶታል ኤንጂኦርአር-ቢፒ 355 ዳካር፣ በንግድ እና የግል ንብረት ብድር ምዝገባ (አርሲሲሰኤም) በቁ ኤስኤን-ዲኬአር 7977 ቢ1976 የተመዘገበ
- ቶታል ሳውዝ አፍሪካ (ፒቲዋይ) ሊሚትድ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማሕበር፣ በደቡብ አፍሪካ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 3 ቶታል ሃውስ፣ ቢርማን ጎዳና፣ ሮዝባንክ 2196 ጆሃንስበርግ፣ በኮርፖሬት ምዝገባ ቁ 1954/003325/07 የተመዘገበ
- ቶታል ታንዛኒያ ሊሚትድ፣ በአክስዮኖች የተወሰነ ማሕበር፣ በታንዛኒያ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ምሳሳኒ ፔኒንሱላ፣ ኃይለስላሴ መንገድ፣ የብሎክ ቁጥር 1፣ ፕሎት ቁ 1720፣ ዳሬሰላም፣ ዳሬሰላም ውስጥ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ 4506 የተመዘገበ
- ቶታል ማርኬቲንግ ቻድ ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር (ሶሳይቴ አኖኒሜ)፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ዞን ደ ሃይድሮካርበርስ፣ ፋርቻ፣ ንጃሚና፣ በንግድ ምዝገባ ቁ 8/8/76 የተመዘገበ
- ቶታል ቶጎ ኤስኤ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር (ሶሳይቴ አኖኒሜ)፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 59 ቦልቫርድ ደ ለ ፔክስ፣ ሎሜ፣ በንግድ ምዝገባ አርሲሲኤም ቁ 1976 ቢ 666 የተመዘገበ
- ቶታል ቱኒዝ ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር (ሶሳይቴ አኖኒሜ)፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ሩ ዱ ላክ ሁሮን-ለ በርግስ ዱ ላክ 1053፣ቱኒዝ፣ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ ቢ14 1611996 የተመዘገበ
- ቶታል ዩጋንዳ ሊሚትድ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ ማሕበር፣ በዩጋንዳ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ ፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ ፕሎት 4፣ ስምንተኛ መንገድ ኢንዱስትሪያል አካባቢ፣ ካምፓላ፣ በንግድ እና ድርጅቶች ምዝገባ በቁ3183 የተመዘገበ
- ቶታል ዛምቢያ ሊሚትድ፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር ፣ በዛምቢያ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፣ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ የፕሎት ቁ 1708/9 ሙንጉዊ መንገድ፣ ኢንዱስትሪያል አካባቢ፣ መ.ሳ.ቁ 31721፣ ሉሳካ፣ በምዝገባ ቁ 366 የተመዘገበ

- ቶታል ዚምባብዌ ፧ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር ፧ በዚምባብዌ ሕጎች መሠረት የተቋቋመ፧ የተመዘገበ የቢሮ አድራሻ 1 ኦክላንድ መንገድ-መ.ሳ.ቁ 2994-ሐራሬ-ዚምባብዌ፧ በምዝገባ ቁ 46560 የተመዘገበ